ቅዳሜ፣ ታኅሣሥ 13 ቀን 20055 ዓ.ም

Dec. 22, 2012

## ዝምታው እስከ መቼ? ወተትም እኮ ይሸፍታል!

ከጨርግደው

ጥንታዊና ታሪካዊት ኢትዮጵያ ነኝ
ልጆቼ! አዱነኝ፣ ˜ረ ተው አድኑኝ
እስከ መቼ? አታዋርዱኝ
እርስ በርስ መጠላለፉን አቁማችሁ
ተባበሩ፣ ተባበሩ ለሕዝቤ ብላችሁ
ሀሁና ABCD አስተምሬ
እንዴት እንዲህ ታደርጉኛላችሁ ፈሪና ጦም አዳሪ?
ወያኔ/ኢሕአዴግ በኤንቬስትመንት ሥም ሸጠው፣ ቸብችበው ጨረሱኝ
አርሶ አደር ልጆቼን አፈናቀሉብኝ፤ ብለውም ጭሰኞች አደረጉብኝ
ሴት ልጆቻችንም አረብ አገር እየላኩና እየሸጡ አዋረዱኝ
ጎጠኞቹና አሲዳሞቹማ ሁን ብለው የወላድ መካን ሊያደረጉኝ
እንዴት ዝም ትላላችሁ? የጥፋት መልክተኞች አጋድመው ሲግጡኝ
ከድርጅት በፊት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እንደሚበልጥባችሁ አውቃችሁ እንዲሁም ተገንዝባችሁ
ወቅቱ ነው! ተነሱ እንነሳ እባካችሁ
ወቅቱ ነው! ተነሱ እንነሳ እባካችሁ

በሀቀኛ ልጆቿ ብቻ ኢትዮጵያ ዳግም ትነሣለች!
ድል ለሕዝባችን!